# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 325 ሐምሌ 25 2006


የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ወጣት፣ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ገበሬ እና በየቦታው ያላችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ! አሸባሪህ ወያኔና ወያኔ ብቻ መሆኑን አውቀህ በገዛ ሀገርህ ላይ ነጻነት በተመኘህና በጠየቅህ ጊዜ ሁሉ ለሽብር ጥቃቱ ኢላማ ያደረጉህን ወያኔ ተባብረን ከላያችን ለማውረድ ተነስ! በያለህበት እምቢ በል! ለወያኔ የሚጠቅም የመሰለህን ነገር ሁሉ አታድርግ! አትተባበር! ሸቀጣቸውን አትግዛ! ወያኔዎችን ከማህበራዊ ሂወትህ አግል! የቻልክ ሁሉ ደግሞ የነጻነት አርበኞችን ዛሬ ነገ ሳትል አሁን ተቀላቀል!!!

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## አንድ የአሜሪካ ሴኔተር ወያኔ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ባስቸኳይ እንዲፈታ ጠየቁ

የአሜሪካ ምክር ቤት የውጭ ጉዳዮች ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ሴናተር ዳና ሮህራባቸር የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌን በፍጥነት እንዲፈታ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሐምሌ 22/2006 ዓ.ም መጻፋቸውን አስታወቁ። የየመን መንግስት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን አለማቀፍ ህግን በተላለፈ ሁኔታ ለፋሽስቱ ወያኔ አሳልፈው መስጠታቸውን በማውሳት አገዛዙ የእንግሊዝ ዜግነት ያላቸውን የፖለቲካ አመራር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መልቀቅ ይኖርባታል ሲሉ አሳስበዋል።

የካሊፎርንያ ሪፓብሊካን ወኪል እና የአሜሪካ ምክር ቤት የውጭ ጉዳዮች ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት ሮህራባቸው የፋሽስቱ ወያኔ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይና በሌሎች ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ እንዲሰፍን በሚታገሉ ሃይሎች ላይ የሚፈጽመውን ኢሰብአዊ ድርጊት በማውገዝ አገዛዙ በነፃነት ታጋዮች ላይ እያደረሰ ያለው ህገ ወጥ የስቃይ እርምጃ በሁለቱ አገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት እንዳሻከረው በይፋ በፃፉት ደብዳቤ አመልክተዋል። የጉጅሌው ወያኔ ሹማምንት በአገሪቱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እያባባሱ ይገኛሉ ሲሉ ወቀሳቸውን ሰንዝረዋል። ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ጋምቤላ ዉስጥ የወያኔ ጎሳ ፖለቲካ የ17 ሰዎች ህወይት ቀጠፈ

በጋምቤላ ክልል በመዥንገር ዞን በመዥንግርና በአካባቢው ለረጅም አመታት በሰፈሩ የአማራ ተወላጆች መካከል አካባቢውን ለቃችሁ ውጡልን በሚል በተነሳ ግጭት 17 ሰዎች መገደላቸውን ለማወቅ ተችሏል። ግጭቱ አሁንም ድረስ እንደቀጠለ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በአማራ ተወላጆች ላይ እየተወሰደው ያለው እርምጃ ለየት ያለና የፋሽስቱ ወያኔ ፖለቲካ ድጋፍ ያለው እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል። እንደምንጫችን ዘገባ ለረጅም ጊዜያት የኖሩበትን አካባቢ ለመልቀቅ ፈቃደኛ ባልሆኑ የአማራ ተወላጆች ላይ ግድያው መፈጸሙን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የሟቾቹ አስከሬኖች በወቅቱ ለማንሳት ባለመቻላቸው በየሜዳው ተጥለው መቆየታቸውን የአይን እማኞች ለዘጋቢያችን አመልክተዋል፡፡ በሁለቱ አካላት መካከል ግጭቱ እንዲፈጠር የተደረገው ሆን ተብሎ በፋሽስቱ ወያኔ የአካባቢው ቅጥረኞች ቆስቋሽነት እንደሆነም ታውቋል።

## ፋሽስት ወያኔ በአንዳርጋቸው ፅጌ ዙሪያ ያቀናበረውን የቅጥፈት ድራማ ለእይታ አበቃ

የፋሽስቱ ወያኔ ልሳን በሆነው ቴሌቪዥን የፖሊስና ህብረተሰብ ፕሮግራም የቀረበውና በተለያዩ ቀናቶች የተቀረጹ ምስሎችን በማቀናበር ለአገዛዙ ፕሮፖጋንዳ እንዲመች ተደረጎ የተሰራው የቅጥፈት ድራማ ለእይታ መብቃቱን ተከትሎ በርካታ ኢትዮጵያውያን ቁጣን ያዘሉ ትችቶችን እየሰነዘሩ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በበርካታ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ አናጤ ሱሪ አስር ቦታ ተለጣጥፎ የቀረበ፤ እንደ ወትሮው ሁሉ በቅጥፈት ብቻ የተሞላ የፋሽስቱ ወያኔ ድራማ የ 8 ደቂቃ ከ 54 ሴኮንድ እርዝማኔ ሲኖረው ድራማው የፋሽስቱ ወያኔ በእስር ቤት በንጹሃን ዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለውን ወንጀልም ያጋለጠ ነበር። በድራማው 53 ኛ ሰከንድ፤ በ 1 ደቂቃ ከ 3 ሰከንድ፤ በ 1 ደቂቃ ከ 7 ሰከንድ እንዲሁም በ 1 ደቂቃ ከ 38 ሰከንድ አቶ አንዳርጋቸው እየተቀረጹ በነበሩበት ወቅት በሌላ ክፍል ግርፋትና ሰቆቃ የሚፈፀምበት ግለሰብ የጣር ጩኸት ሲያማል ይደመጣል። ይህን የሰቆቃ ጩኸት በማስረጃነት ኢትዮጵያውያን ለዓለም አቀፍ መንግስታትና የሰብአዊ መብት ድርጅቶች በማቅረብ ፋሽስቱ ወያኔ በእስር ቤቶች ውስጥ በንፁሃን ዜጎች ላይ እየፈጸመ ስላለው ሰቆቃ ለማሳወቅ ሊቀርብ የሚችል ተብሎለታል።

አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ለሁለተኛ ጊዜ ቃላቸውን ሰጡ በማለት በየ 50 ሴኮንድና አንድ ደቂቃ ልዩነት የተቆራረጠና ኤዲት የተደረገ፤ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## ወያኔ አንዳርጋቸው ጽጌ ደብረዘይት አየር ሃይል ግቢ ወስዶ እያሰቃየ ነው

የግንቦት7 ዋና ጸሃፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ከሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም. ጀምሮ ደብረዘይት በሚገኘው የአየር ሃይል ግቢ ውስጥ በአንድ አነስተኛ ክፍል ውስጥ ታስረው ከፍተኛ ስቃይ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ የኢሳት ምንጮች ገልጸዋል። ኢሳት የተለያዩ ምንጮችን አነጋግሮ ባሰባሰበው መረጃ አቶ አንዳርጋቸው በመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ከፍተኛ ድብደባ ከተፈጸመባቸው በሁዋላ ድበደባው ቆሞ፣ የማሰቃያ መርፌዎችን እየተወጉና በኤልክትሪክ ሾክ እየተሰቃዩ መረጃ እንዲያወጡ እየተገደዱ ነው። መርማሪዎች ከአቶ አንዳርጋቸው የሚፈልጉት መረጃ ከግንቦት7 ጋር በጋራ የሚሰሩ አሁን በስልጣን ላይ ያሉ የኢህአዴግን አመራሮችን እንዲሁም በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ያሉ አዛዦችን ስሞች ሲሆን፣ አቶ አንዳርጋቸው ግን እስካሁን ምንም አይነት መረጃ ባለመስጠታቸው፣ መርማሪዎች ሲበሳጩ መታየታቸውን የኢሳት ምንጮች ገልጸዋል። ለወትሮው አንድ መረጃ ሲያገኙ በታላቅ ደስታ የሚፈነጬት መርማሪዎች፣ ምርመራቸውን ጨርሰው ሲወጡ የሚያሳዩት ብስጭት፣ እስካሁን ድረስ የሚፈልጉትን እንዳላገኙ የሚያሳይ መሆኑን ጉዳዩን በቅርበት የሚከታተሉ ምንጮች ገልጸዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ዘረኛዉ ወያኔ ለኢድ አልፈጥር በአል የደገሰዉን የጥፋት ድግስ ድምፃችን ይሰማ አከሸፈዉ

1 ሺህ 435ኛው የኢድ አልፈጥር በመላው የእስልምና ተከታዮች ዘንድ የተከበረ ሲሆን በአዲስ አበባ ስታዲየም ድምጻችን ይሰማ ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳይካሄድ ባዘዘው መሰረት፣ ተቃውሞ ሳይካሄድ ቀርቷል። በዒድ አልፈጥር በዓል ፋሽስቱ ወያኔ ህዝበ ሙስሊሙን ለመጨፍጨፍ እንደተደራጀ መረጃ ቀድሞ የደረሰው ድምፃችን ይሰማ ተቃውሞውን መሰረዙ ታውቋል። የጉጅሌው ወያኔ መጅሊስ ካድሬዎች ንግግር የታከተው የአዲስ አበባ ህዝበ ሙስሊም ወደ አስታዲየም ባለመሄድና እስታዲየሙን ባዶ በማድረግ ታላቅ መልዕክት ማስተላለፉንም ዘጋቢያችን ከአዲሳባ የላከልን መረጃ ያመለክታል።

ስታዲየም ላይ በጥቂት ግለሰቦች ማለትም መኖሪያቸው ለስታዲየም ቅርብ የሆነና ሌላ አማራጭ መስገጃ የሌላቸው የእስልምና እምነት ተከታዮች የተገኙ ሲሆን በስነስርዓቱ ላይ የህገ-ወጡ መጅሊስ ፕሬዝዳንት ተደርጎ በጉጅሌው ወያኔ የተሾመው አህመድ አብዱረህማን ንግግር ያደረገ ሲሆን፤ የአዲስ አበባ ከንቲባ ድሪባ ኩማ የፕሮፓጋንዳ መልዕክት በተወካይ ቢነበብ ህዝበ ሙስሊሙ ለመልዕክቶቹ ጆሮ ባለመስጠት ለአምላኩ ጸሎቱ ሲያደርስ እንደነበር የአይን እማኞች ተናግረዋል። ስታዲየሙ ያልተገኘው ብዙሃኑ የአዲስ አበባው ህዝበ ሙስሊም ጸሎቱን በቤቱ በማድረስ፤ የታሰሩ ጀግኖቻቸውን በማሰብ፤ እንዲሁም በአገዛዙ እና በሆድ አደር ካድሬዎቹ ላይ ያለውን መራር ተቃውሞና መልዕክት በማስተላለፍ ታሪክ ሰርቶ መዋሉም ተዘግቧል።

## ብአዴን ወጣቶችን "በጸረ ሰላም ሃይሎች" ላይ እርምጃ ዉሰዱልኝ ሲል ተማጸነ

የወያኔዉ ተለጣፊ የሆነዉ ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ብአዴን) በወጣቶች ሊግ ስር፤ በአንድ ለአምስትና በስራ ዘርፍ በየቦታዉ ያደራጃቸዉን ወጣቶች "ጸረ ሰላም ኃይሎችን" ካልደመሰሳችሁ ህልዉናችሁ አደጋ ላይ ነዉ ሲል አስጠነቀቀ። በከተሞች የሚገኙ አውራጅና ጫኝ ፤ሊስትሮ፤ ሱቅ በደረቴ፤ ተጽእኖ ፈጣሪ ወጣቶችን፤ በተለያዩ አደረጃጀቶች የታቀፉ ወጣቶችን እና በአደረጃጀት ያልታቀፉ ሌሎች ወጣቶችን በወቅታዊ ጉዳዮች ዙርያ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀው ሰነድ፣ "የጥፋት ፖለቲከኞች እንቅስቃሴ በመላ የከተማችን ሰላም ወዳድ ወጣቶች የተደራጀና የነቃ ተሳትፎ እንዲከሽፍ ካልተደረገ በመላ ቀልቡ ወደ ልማቱ የገባው ህዝባችን በተለይ ደግሞ ተጠቃሚ እየሆነ የመጣው ወጣቱ ከልማት ተግባሩ ሊስተጓጎል ይችላል" ሲል አስጠንቅቋል።በብአዴን የተዘጋጀው ሰነድ ለኢሳት የደረሰ ሲሆን፣ በሰነዱ ላይ የጥፋት ሃይሎች የተባሉት አካላት በስርአቱ ላይ ከባድ ፈተና መደቀናቸውን አትቷል። ሰነዱ የጥፋት ሃይሎቹ " የመጀመርያው በአማራ ህዝብ ላይ የተለያየ የጀግንነት ስም እየሰጡ ከሌላው ብሄር ጋር ተቻችለን ተከባብረን በልዩነታችን ውስጥ አንድነትን እንዳንመሰርትና ከሌሎች ብሄር ወንድሞቻችን ጋር ተቻችለን እንዳንኖር የትምክህትን እና ፀረ-ዲሞክራሲያዊ የሆነ ቅስቀሳቸውን በማራገፍ በተለይም ለዚህ ድብቅ አላማቸው ወጣቶችን መጠቀሚያ መፈለጋቸውን፣ ይህም በቅርቡ በመላው ኢትዮጵያ ስፖርት ጨዋታ ላይ የታየው ምልክት የሚጠቀስ ነው" ብሎአል። ይጥፋት ሃይሎች" ከጦር የተመለሱ ታጋዮች ልዩ ድጋፍ አልተደረገላቸውም፣ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የህወሃት ሽብር መቆም አለበት!

ዛሬ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ያለ አሸባሪ ወያኔና ወያኔ ብቻ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሰዎችን በፖለቲካ አመለካከታቸው፣ መንግስት በመተቸታቸው በግልጽ በመጻፋቸውና በአደባባይ በመናገራቸው ከዚህም አልፎ በጥርጣሬ በተለይም በብሄረሰብ ማንነታቸው እያሳደደ የሚያፍን የሚያሰቃይና የሚገል የሽብር ተቋም ካለ ወያኔ ብቻ ነው። በኢትዮጵያ መሬት ላይ ሰላማዊ ዜጎችን ኢላማ ያደረገ የተቃውሞ ሃይል በተግባርም ሆነ በአስተሳሰብ ከወያኔ ውጪ አንዳች ሃይል የለም።

አፋኙ የወያኔ ስርአት በተለየም የህዝቡን ሀብትና ንብረት እየዘረፉ የሚቀማጠሉት የህወሃት መሪዎችና ሎሌዎቻቸው የተቃውሞ ድምጽ በሰሙ ቁጥር እንደሚሸበሩና እንቅልፍ አጥተው እንደሚያድሩ ይታወቃል። አፍነውና ዘርፈው ገለው የሚገዙት ህዝብ ግፍ በዛብኝ ብሎ በተናገረ ቁጥር የሚሸበሩት እነሱ ብቻ እንጂ ህዝቡ አይደለም።

በኢትዮጵያ ምድር ያለው አሸባሪ ወያኔ ብቻ መሆኑን ሺ ምሳሌዎችን ጠቅሶ ማስረዳት ይቻላል። ሶስት አመት ሙሉ የሰላም እጃቸውን እየዘረጉ ከልመና ባልተለየ ሁኔታ መብታቸውን የጠየቁና ድምጻችን ይሰማ ያሉት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ማንንም ዜጋ አላሸበሩም። የተገላቢጦሽ እነሱ አሸባሪ ተብለው የግፍ ሰቆቃ ይፈጸምባቸዋል። ጋዜጠኞችና ጦማሪዎቹ መንግስት ያወጣውን ህግ እንዲያከብር ስለጠየቁ በአደባባይ ስለጻፉ ግፍ ይፈጸምባቸዋል። እነሱ ያሸበሩት ሀገርና ህዝብ የለም። ከመንገድ ላይ ጎትተው እንደ እባብ ቀጥቅጠውና ፈነካክተው በማግስቱ ፍርድ ቤት ያቀረቧት ወየንሸት ሞላ የተባለች ባለ ተስፋ ወጣት የወያኔ አረመኔዎች በሙስሊሙ ህዝብ ላይ የሚሰሩትን ጭፍጨፋ እግር ጥሏት ከማየትና ከመታዘብ ውጪ ያሸበረችው ሰው፣ ሀገር የለም። በየወህኒ ቤቱ እና አፈና ጣቢያው ታስረው የሚቀጠቀጡት የኦሮሞ ልጆች ለጥያቄያቸው መልስ ሲጠብቁ ከመጨፍጨፍ ያለፈ የፈጸሙት እብሪት የለም። በየክልሉ ቀና ብለህ ባለስልጣን ተናገርክ፣ ጥያቄ ጠየቅክ፣ ባለስልጣን ደፈርክ፣ ተሰብስበህ አየንህ ወዘተ እየተባለ የሚገረፈው እንደ እንስሳ እየተገደለ የሚጣለው ገበሬ የሰራው ወንጀል የለም። አሸባሪም አይደለም! በየቦታው ቦንብ እየቀበረ አፈንድቶ ንጹሃንን ገድሎ ሊያፈነዱ ሲሉ ፈንድቶባቸው ራሳቸውን ገደሉ ብሎ በአደባባይ የሚሳለቀው አሸባሪው ህወሃት እንጂ ንጹሃኑ አይደለም።

የኛ መሪ አንዳርጋቸው ከልጅነት እድሜው ጀምሮ ራሱን ለህዝብ ነጻነት የሰጠ አርበኛ እንጂ አሸባሪ አይደለም። በተመሳሳይ ውንብድና ከጎረቤት ሀገር ድረስ በአለም አቀፍ የወረበሎች ውንብድና መንገድ ወያኔ እያፈነ የገደላቸው አሮሞዎችና፣ ሱማሌዎች፣ አኙዋኮች፣ አማሮችና ሌሎችም ነጻነት ከመፈለግ ውጪ ያሸበሩት ህዝብና ሀገር የለም።

በኢትዮጵያ ምድር የነጻነት ድምጽና ኮሽታ በሰማ ቁጥር የሚሸበረው ህወሃትና በለሟሎች ብቻ ናቸው። ይህ የነጻነት ድምጽ ደግሞ እየጎላ መሄዱ የማይቀር ነውና ወያኔ ሰፈር ሽብር ይሆናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ! ወጣት፣ ሴት፣ ሽማግሌ፣ ገበሬ እና በየቦታው ያላችሁ የኢትዮጵያ ልጆች ሁሉ! አሸባሪህ ወያኔና ወያኔ ብቻ መሆኑን አውቀህ በገዛ ሀገርህ ላይ ነጻነት በተመኘህና በጠየቅህ ጊዜ ሁሉ ለሽብር ጥቃቱ ኢላማ ያደረጉህን ወያኔ ተባብረን ከላያችን ለማውረድ ተነስ! በያለህበት እምቢ በል! ለወያኔ የሚጠቅም የመሰለህን ነገር ሁሉ አታድርግ! አትተባበር! ሸቀጣቸውን አትግዛ! ወያኔዎችን ከማህበራዊ ሂወትህ አግል! የቻልክ ሁሉ ደግሞ የነጻነት አርበኞችን ዛሬ ነገ ሳትል አሁን ተቀላቀል!!! ነጻነታችን ያለው በእጃችን ላይ መሆኑን አትዘንጋ። ግንቦት 7 ሁልጊዜም ከመቼውም ጠንክሮ ከጎንህ ነው።

የወያኔን ሽብር በተባበረ ሃይል እናቁመው!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## የኢድ አልፈጥር በዓል በመላው የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ተከብሮ ዋለ

1 ሺህ 435ኛው የኢድ አልፈጥር በመላው የእስልምና ተከታዮች ዘንድ እየተከበረ ነው። በአዲስ አበባ ስታዲየም የነበረው ክብረበአል በሰላም የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ድምጻችን ይሰማ ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳይካሄድ ባዘዘው መሰረት፣ በአዲስ አበባ ስታዲዮም ተቃውሞ ሳይካሄድ ቀርቷል። የኢህአዴግ የጸጥታ ሃይሎች ሰሞኑን በወሰዱት ጠንካራ እርምጃ በርካታ ሙስሊሞች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን፣ ቁጥራቸው በውል ያልተወቀ ሙስሊም ዜጎች በእስር ቤት እየማቀቁ ይገኛሉ። በኢድ አል ፈጥር ላይ ተቃውሞ ከተነሳ የኢህአዴግ ደህንነቶች እርምጃ ለመውሰድ ተዘጋጅተው እንደነበር መዘገቡ ይታወሳል። ልቁማን የኢትዮጵያ ቤልጂየም የሙስሊም ማህበር (ልብማ) ለኢሳት በላከው መግለጫ መንግስት ባለፈው አርብ በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰደውን እርምጃ አውግዟል።

ማህበሩ በመግለጫው ህዝበ ሙስሊሙ ላነሳቸው የመብት ጥያቄዎች የመንግስት ምላሽ ግድያ፣ ድብደባ፣ እስራትና ንቀት መሆኑን አስታውሷል። የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ጨምሮ በሺዎች የሚቆጠሩ መታሰራቸውን፣ ብዙ ንጹህ ሙስሊሞች መገደላቸውን፣ አንዳንዶች አገር ጥለው መሰደዳቸውን እንዲሁም ሌሎች አካል ጉዳተኞች ቆነው መቀመጣቸውን ጠቅሷል። የሙስሊሙ ማህበረሰብ ትግሉን ከመቀጠል ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለው ልብማ ጠቅሶ፣ ድምጻችን ይስማ በኢትዮ-ቴልኮ ላይ የጣለውን የአንድ ቀን ማእቀብም በማድነቅ ተመሳሳይ እርምጃዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቋል። በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ከሙስሊሞች ጎን እንዲቆሙ፣ መላው የኢትየጵያ ህዝብም በሚወሰዱት እርምጃዎች ተባባሪ እንዲሆን ማህበሩ ጥሪ አቅርቧል።

## ወያኔ አንዳርጋቸው ጽጌ ደብረዘይት አየር ሃይል ግቢ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

አቶ አንዳርጋቸው እንዳስፈላጊነቱ በቀን ሶስት ጊዜ ምርመራ እንደሚካሄድባቸው የሚናገሩት ምንጮች፣ ምርመራውን የሚያካሂዱት የተመረጡ የህወሃት የደህንነት ሰራተኞች መሆናቸውንና በግቢው ለበረራ የሚሰለጥኑ የሌሎች ብሄር ተወላጆች ወይም የደህንነት ሰራተኞች ወደ አካባቢው እንደማይሄዱ ገልጸዋል። ምሽት አካባቢ የሚሰማው የጣር ድምጽ የሚረብሻቸው የእለት ተረኛ ጠባቂ መኮንኖች በሁኔታው እያዘኑ አንዳንዶች ስሜታቸውን መቆጣጠር እንደማይችሉ ምንጮች አክለው ገልጸዋል። ስለ አቶ አንዳርጋቸው የእለት ውሎ ማወቂያ ብቸኛው ዘዴ የመርማሪዎች ፊት ነው የሚሉት ምንጮች፣ እስካሁን ድረስ ምርመራ በሚያካሂዱ የህወሃት አመራሮች ዘንድ የደስታ ፊት እንደማይነበብ ገልጸዋል።

የኢህአዴግ መንግስት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ የታሰሩበትን ቦታ ይፋ ለማድረግ እስካሁን ፈቃደኛ አልሆነም። የእንግሊዝ ባለስልጣናት ለአቶ አንዳርጋቸው የኮንሱላር የማማከር አገልግሎት ለመስጠት ጥያቄ ቢያቀርቡም ኢህአዴግ ባለስልጣናት ፈቃደኛ አልሆኑም። ከዚህ በተቃራኒ ኢህአዴግ በአቶ አንዳርጋቸው እና በግንቦት7 ላይ ለሚሰራው ድራማ ግብአት ይሆን ዘነድ የተለያዩ ሰዎችን ማሰማራቱን ምንጮች ገልጸዋል። ቀደም ብለው በአገዛዙ ለስለላ ወደ ኤርትራ ተልከው እና ለተወሰኑ ወራት ግንቦት7 ትን ተቀላቅለው በመጨረሻ የኢህአዴግ የስለላ አባላት መሆናቸው ሲታወቅ የጠፉ እንዲሁም ፈንጅ ሊያፈነዱ ሲሉ ተያዙ የተባሉ እና በእስር ላይ የሚገኙ ሰዎችን ለመጠቀም እንቅስቃሴ መጀመሩን ለማወቅ ተችሎአል። የኢትዮጵያ ህዝብ በአቶ አንዳርጋቸው መያዝ ያሳየው ቁጣ ያስደነገጣቸው ደህንነቶች ለማንኛውም በሚል በደንበር አካባቢ ጥበቃቸውን እያጠናከሩ ነው።

የአቶ አንዳርጋቸውን መያዝ ተከትሎ ግንቦት7ትን የሚቀላቀሉ ሰዎች መጨመራቸውንም ከድርጅቱ የወጣው መረጃ ያመለክታል።ይህ በእንዲህ እንዳለ በቤልጂየም ብራሰልስ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ኢህአዴግ አቶ አንዳርጋቸውን ለመያዝ የሄደበትን እርቀት ከማውገዝ በተጨማሪ የእንግሊዝ መንግስት የአቶ አንዳርጋቸውን ጉዳይ አጥብቆ እንዲከታተል ጠይቀዋል። ኢትዮጵያውያኑ ዛሬ በአውሮፓ ህብረት ቆንስላ ጽ/ቤት ፊት ለፊት የተቃውሞ ድምጻቸውን በከፍተኛ ቁጣ ከማሰማት በተጨማሪ፣ ያዘጋጁትን ደብዳቤ ለአውሮፓ ህብረት ባለስልጣናትና ለእንግሊዝ መንግስት ኮንስላ ጽ/ቤት ሃላፊዎች አስረክበዋል።

## ሠራዊቱ የህዝብ ወገንተኛነቱን የሚያስመሰክርበት ግዜ እየመጣ ነው

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የቀደመው ትውልድ ከቱርክ ኤምፓየር፤ ከግብፅ እና ከደረቡሽ፤ ከጣሊያን ወራሪ፤ ከሶማሊያ ተስፋፊ ኃይል እና ከሌሎችም የኢትዮጵያ ጠላቶች ጋር ተዋግቶ አገሪቷን ለአሁኑ ትውልድ ለማቆየት ትልቅ መስዋዕትነት ከፍሏል። በተለይ ነፍጥ አንግቦ የተሠለፈው ኃይል የከፈለው የህይወት መሥዋዕትነት የሚረሳ አይደለም። አገራችን ኢትዮጵያ ለዛሬው ትውልድ የቆየችው ከራሱ ይልቅ ለአገርና ለወገን የሚያስብ ትውልድ በመኖሩ መሆኑ የሚያከራክረን ጉዳይ አይሆንም።

የአገር መከላከያ ሠራዊት እና የአገር ደህንነት ኃይል የቆመው አገርን ከጥቃት ለመከላከል ነው። አገር በጠላት እጅ ወድቃ በወገን ላይ ስቃይ እንዳይደርስ፤ ህዝቡም አገር አልባ እንዳይሆን መጠበቅ የአገሪቷ የሠራዊትና የደህንነት ኃይል ዋና ተግባር ነበር። ህወሃት መራሹ መንግስት አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያ ሥም የቆመው ሠራዊት እና የደህንነት ኃይል ተግባሩ ሌላ ሁኗል።

በዚህ ዘመን ሠራዊቱና የደህንነት ኃይሉ የአገርን ብሄራዊ ደህንነት የሚጠብቅ ሳይሆን ህወሃት የተባለውን ዘረኛና ዘራፊውን ቡድን የሚጠብቅ ኃይል መሆንን እንዲመርጥ ሁኖ አገርን ከጠላት የመከላከል ተግባሩን ረስቷል። ይህን ኃይል የሚመሩትም ደማቸውንና አጥንታቸውን ቆጥረው ከአንድ መንደር/ጎሣ የተሰባሰቡ እና ካርታ ይዘው የቆሙበትን ሥፍራ እንኳን ለመለየት የማይችሉ መሃይማን መሆናቸው አገሪቷ ያለችበትን አደጋ ከሚያመላክቱ ምልክቶች መካከል አንዱ ነው። ህወሃቶች የደርግ ሠራዊት እያሉ ሊሳለቁበት የሚሞክሩት የቀድሞው የአገሪቷ መከላከያ ኃይል ሲመራ የነበረው አውሮፓና አሜሪካን ድረስ ተጉዘው በተማሩ፤ ማዕረጋቸውም የዓለም ዓቀፉን ደረጃ የጠበቀ፤ አገሪቷን ወክለው አደባባይ ቢወጡ የሚያኮሩ እንደነበረ የታወቀ ነው። የሹመታቸው መሠረትም ደምና አጥንት ሳይሆን እውቀታቸው፤ ችሎታቸውና ወታዳራዊ ብቃታቸው ነበረ።በህወሃት የሚመራውን ሠራዊትና የደህንነት ኃይል የሚመሩት ቡድኖች ከቀድሞዎቹ ሥርዓት የጦር መሪዎች ጋር ሲወዳደሩ የጫማቸውን ጠፍር እንኳ ለመፍታት የሚታጩ አይሆኑም።ግዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል እንደሚባለው ሆነና ጨካኞችና ነፍሰ ገዳዮች በወንበሩ ቁጭ ብለው የአገሪቷን ውድቀት እያፋጠኑት ይገኛሉ።

ዛሬ ህወሃቶች በወንበሩ ቁጭ ብለዋል። እነዚህ ከጭካኔ በቀር እንጥፍጣፊ የአገር ፍቅር የሌላቸው ቡድኖች አቋቋምን ያሉት ሠራዊትና የደህንነት ኃይልም አገሩንና ወገኑን ከመጠበቅ ይልቅ የገዛ ወገኑን የሚያሸበር ቡድን እንዲሆን ተደርጓል። ሠራዊቱ እና የደህንነት ኃይሉ ለአገርና ለትውልድ እንዲያስብ ሳይሆን የጥቂት ዘረኞችን ዕድሜ ለማራዘም ዘብ የቆመ ኃይል እንዲሆንም ሁኗል። ህወሃት እየፈጠረ ያለው ሠራዊትና የደህንነት ኃይል በጀግና ማዕረግ አገሩንና ህዝቡን ከጥቃት ተከላክሎ በህዝቡ ተከብሮና ተወዶ እንዲኖር ሳይሆን በጭካኔው ታውቆ እና የወገኑን ፍቅር አጥቶ በስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ የሚኖርን ኃይል ነው። እንዲህም ሁኖ በመቀረፁ ግደል ሲባል ገስግሶ ሂዶ የገዛ ወገኑን ይገድላል። አፍርስ ሲባል ፈጥኖ በብዙ ድካምና ወጪ የተገነባውን የወገኑን መኖሪያ ቤት ያፈርሳል። እሠር ሲባል ህፃን ከአዛውንት ሳይለይ ያገኘውን ሁሉ ወደ ወይኒ ቤት ያግዛል። በእንዲህ ሁኔታ ከወገኑ ተለይቶ፤ በወገኑ ላይ ዘምቶ፤ ወገኑን ወግቶ፤ ወገኑን አሥሮና አሰቃይቶ ራሡም እንደገና በክፉ ድርጊቱ ታሥሮ እንዲኖር ሁኗል።

ህወሃት የፈጠራችሁ እና በአገር መከላከያ እና ደህንነት ኃይል ሥም ቁማችሁ በወገኖቻችሁ ላይ እንድትዘምቱ የተደረጋችሁ የሠራዊቱና የደህንነት ኃይሎች አድምጡ። አሁን አገራችን ባለችበት ሁኔታ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ዋነኛው ጠላት ህወሃት ነው። ህወሃት የዘረኞችና የዘራፊዎች ስብሰብ ነው። የዘረኝነታቸው መገለጫ ብዙ ነው። የሚያዙህ ጄኔራል ተብየዎች ደማቸውን ቆጥረው የተጫኑብህ መሆናቸውን ተመለከት። እነዚህ ጄኔራሎች አገሪቷን ከተቆጣጠሩ ዘመን ጀምሮ ያካበቱትን የሃብት ብዛት ተመልከት። ሁሉም በሚሊዮን የሚቆጠር ሃብት ባለቤት ናቸው። ልጆቻቸው በአውሮፓና በአሜሪካን ይማራሉ። ሚስቶቻቸው አውሮፓና አሜሪካን እየሄዱ እንዲወልዱ ይደረጋል።ይሄን ለምን ያደርጋሉ ቢባል እየገዙ ያሉት አገር የራሳቸው አገር ስለመሆኗ ብርቱ ጥርጣሬ ስላላቸው ነው። ህዝቧንም እንደ ወገኖቻቸው ለማየት ሥር የሰደደ ጥላቻማላቸው። አንተ እና ወገኖችህ ግን ከሙታን ትንሽ ከፍ ብላችሁ፤ ከሚኖሩት እገር ሥር ተረግጣችሁ የህወሃቶች አኗኗሪ ሁናችሁ የመከራውን ዘመን ትቆጥራላችሁ። በድህነት የሚወቅሯችሁ እንሷቸው ይሄና አስባችሁ፤ ያንን ተናገራችሁ እያሉ በዓለም ላይ በተከለከለ የቶርቸር ዓይነት እንድትሰቃዩ ትደረጋላችሁ። ይህ የጠላት ተግባር ነው።አሁን ባለንበት ዘመንም የኢትጵያ ዋነኛው ጠላት ህወሃት መሆኑን ያለምንም ጥርጣሬ ማመን ይኖርባችኋል።

ህወሃትን ጠላት የሚያድረገው ምንድ ነው ?

ህወሃቶች ወደ ስልጣን ከመጡ ዘመን ጀምሮ ሁለት ሚሊዮን አማራ ጠፍቷል። ይሄ ሁሉ አማራ የት እንደገባ ህወሃት እስከ አሁን አልተናገረም። ይሄ ዘረኛ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ በዜጎች መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን ጠፍቷል። በዚህም ምክንያት ዜጎች ከኖሩበት ሥፍራ እየተነቀሉ ሜዳ ላይ እንዲወድቁ ሁኗል። ይሄ ዘራፊ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ ግዜ ጀምሮ ከአገሪቷ ውስጥ በስምንት ዓመታት ውስጥ ብቻ ከ11 ቢሊዮን ዶላር በላይ ተዘርፎ በውጪ አገራት ባንኮች ውስጥ ተደብቋል። ይህ ቡድን ስልጣኑን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ከአገሪቷ በሚሰደዱ ምሁራን፤ ጋዜጠኞች፤ የኃይማኖት አባቶች እና በሌሎች ዜጎች ቁጥር ኢትዮጵያን የሚያክል አልተገኘም። ህወሃት የተባለው ዘረኛ እና ዘራፊ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ በኋላ አባቶች በደምና አጥንታቸው ያቆዩት ድንበር እየፈረሰ እና ኢትዮጵያዊያን እየተፈናቀሉ ሜዳ ላይ ተጥለው መሬቱ ለባእዳን እየተሰጠ ነው። ይሄ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ድሃ ሜዳ ላይ ተጥሎ የድሃውን መሬት ህወሃቶች እየነጠቁ ባለሃብት ነን ብለዋል። ይሄ ቡድን አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ሃሳብን በነፃ መግለፅ አሸባሪነት ሁኗል። ህወሃትን መንቀፍ በሞት የሚያስቀጣ ወንጀል እስከመሆን ደርሷል። ኢትዮጵያ ይህን በሚመስለው ጠላት እጅ ተይዛለች።

ኢትዮጵያን ከዚህ ጠላት እጅ ለማላቀቅ የሠራዊቱና የአገር ደህንነት ኃይሉ ከፍተኛ ሚና መጫወት አለበት። ከህወሃት የበለጠ ጠላት ኢትዮጵያ የላትም፤ በታሪኳም እንዲህ ዓይነት ጠላት አይታ አታውቅም። ይህን ጠላት ወደ ከርሰ መቃብሩ የሚከት የለውጥ ባቡር እየገሰገሰ ነው። ይሄን የለወጥ ባቡር ፈፅሞ ማቆም አይቻልም። ህወሃቶች የለውጡ ባቡር በፍጥነት እየገሰገሰ እንደሆነ እያዩት ነው። በዚህም አንዳንዶቹ የዘረፉትን ሃብት ይዘው እየሸሹ ነው። ሌሎቹም የሚያደርጉትን አጥተው በዜጎች ላይ በስቃይ ላይ ስቃይ እያበዙ ነው። የሠራዊቱና የደህንነቱ ኃይል የኢትዮጵያዊያን ጠላት መሆንን ከመረጡ ዘረኞች ጎራ ራሱን ለይቶ የህዝብ ልጅ፤ የአገር ጥላ ከለላ መሆኑን አሁኑኑ ማሳየት መጀመር ይጠበቅበታል። የአገር መከላከያ አባል ስትሆን አገርህን ከጠላት ለመከላከል እንጂ ከጠላት ጋር አብረህ የገዛ ወገንህን ስቃይ ለማብዛት አይደለም። ከጠላት ጋር መወገንን ከመረጥክ ግን የተነሳው የለውጥ ባቡር አንተንም ጨፍልቆ እና ታሪክህን ከዘረኞችና ከዘራፊዎች ጎራ ፅፎ እንደሚያልፍ ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ አይኑርህ።

የእኛ እምነት ግን ከህወሃቶች ጎን ቁመህ ወንድሞችህን ትወጋለህ የሚል አይደለም። ህወሃቶች ለአንተ ወንድምም ጋሻም መከታም የሚሆኑ አይደሉም። በአሁን ሠዓት የህወሃቶች ጭንቀት የዘረፉትን ሃብት የሚያሸሹበትን ሥፍራ የማግኘት ነው እንጂ የአንተ ደህንነት አይደለም። ህወሃቶችን እንቅልፍ የሚነሳቸው የሠሯቸው ትላልቅ ህንፃዎች ፍፃሜ እንጂ የኢትዮጵያዊያኑ በሠላም የመኖር ጉዳይ አይደለም። ህወሃቶች የሚሞቱለትም ሆነ የሚኖሩለት አንድ እና አንድ ምክንያት ዘርፈው ያካባቱት ሃብት እንጂ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንዳልሆነች የታወቀ ነው። አንተ የሠራዊቱ አባል ግን የእነዚህን ዘረኞችና ዘራፊ ህወሃቶችን እድሜ ለማራዘም የምትሞተውና የምትገድለው ለምንድ ነው? የእነርሱን እድሜ ለማራዘም ብለህ ብትሞት ለህወሃቶች ወግኖ ኢትዮጵያዊያንን ሲወጋ ሞተ ተብለህ መሳለቂያ ሆነህ መቅረትህን አታውቅምን ?

እኛ ግን እንዲህ እንልሃለን ለአገርህ መሞት ክብር ነው። ለአገር መሞት ማለትም በዚያች አገር ውስጥ ለፍትህ፤ ለህግ የበላይነት፤ ለነፃነት፤ ለእኩልነት እና ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ራስን አሳልፎ መስጠት ማለት ነው።በዚህ ሞትህ ማንም ማንንም ሳይጫን፤ ማንም ማንንም ሳይሸከም መኖር የሚቻልባት አገር ተፈጥራ እኩልነት ሲሰፍን የአንተ ስም በአገሪቷ እስከ ዘላለሙ ሲታወስ ይኖራል። ልጆችህና ልጅ ልጆችህ በአንተ ሥራ ኮርተውና አንገታቸውን ቀና አድርገው የሚሄዱ ይሆናሉ። ለዚህ ዘላቂ ክብር ብለህ ብትሞት ሞትህ የክብር ሞት ይሆናል። የሣሞራንና የጓደኞቹን የሥልጣን ጥም ለማርካት ብለህ ብትገልና ብትሞት ግን አሟሟትህ ከንቱ ይሆናል። ለነፃነት፤ ለእኩልነት እና ለህግ የበላይነት ብለው የተነሱ ነፁሃን ዜጎችን ለመግደል የታጠከውን ነፍጥ ብታነሳ ፍፃሜህ ከንቱ ሁኖ እንደሚቀር አትጠራጠር። የምትሞትለትም ሆነ የምትኖርለት ዋናው ቁም ነገር ሊሆን የሚገባው በህወሃቶች የተጣመመውን ፍትህ ለማቃናት፤ ወገኖችህና አንተ የተነጠቃችሁትን ነፃነት ለመቀዳጀት፤ እውነተኛ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት በአገርህ እንዲሠፍን፤ ጥቂት ዘረኞች ብዙሃኑን ተጭነው፤ ብዙሃኑም እነዚህ ጥቂት ዘረኞችን ተሸክመው የሚኖሩበት ሥርዓት እንዲያበቃ ሊሆን ይገባዋል። ለእነዚህ ድንቅ ሃሳቦች ብለህ ብትሰዋ መስዋዕትነትህ የጀግና መሥዋዕትነት ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ መሰዋዕትነት ለአገርና ለወገን የሚሰጥ ውድ እና ታላቅ ስጦታ ነው። ይሄን ውድ እና ታላቅ ስጦታ የሰጠ ደግሞ በታሪክ ማህደራት ውስጥ ስሙ ለዘላለም ሲታወስ ይኖራልና የለወጡን ባቡር እንድትሳፈር እንመክርሃለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!

## ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተማፅኖ ደብዳቤ ተላከለት

ካለፈዉ መጋቢት ወር ጀምሮ በሽብርተኝነት ተጠርጥረው ለሦስት ተከታታይ ወራት በእስር ላይ የቆዩትንና በቅርቡ በፀረ ሽብርተኝነተ አዋጁ ክስ የተመሠረተባቸዉን ጦማሪያንና ጋዜጠኞች አስመልክቶ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ለጠ/ሚኒስቴር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የተማጽኖ ደብዳቤ መላካቸዉ ታወቀ። ከደብዳቤው ፈራሚዎች መካከል ሂዩማን ራይትስ ዎችና አምነስቲ ኢንተርናሽናል በግንባር ቀደምትነት የሚገኙበት ሲሆን፣ እነዚህ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የሰብዓዊ መብት አያያዝና የፐሬስ ነፃነት የወያኔን አገዛዝ ምንግዜም አንደኮነኑ ነዉ። ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ስልጣን በያዘባቸዉ አመታት ሁሉ ከአመኒስቲ ኢንተርናሺናልና ከሰብዐዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር አንድም ቀን ተስማምቶ የማያዉቅ ሲሆን በተለይ የወያኔ የፀጥታ ኃይሎች ሶማሊያና ኦጋዴን ፈጽመዋል ባሉት የሰብዓዊ መብት ጥሰት ምክንያት ግንኙነታቸው እጅግ ሻክሮ ይገኛል።

ይህ በእንዲህ እንደለ የግንቦት ሰባት ንቅናቄ ዋና ፀሀፊ የሆኑት አቶ አንዳርጋቸዉ ጽጌ በወያኔ አለአግባብ ተይዘዉ የሚደርስባቸዉን ግፍና መከራ በኢትዮጵያዊነቷ ያንገበገባት አንዲት እዚህ አሜሪካ ዉስጥ የምትኖር ታዳጊ ወጣት አቶ አንዳርጋቸዉን ፍቱልኝ ስትል ለጠ/ሚኒስቴር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የተማጽኖ ደብዳቤ መላኳ ከወደ አሜሪካ ተሰማ። በኮሎራዶ ግዛት ሴንቲኒያል ከተማ የምትገኝ አንዲት የ 10 አመት ታዳጊ ልጅ ያቶ አንዳርጋቸው ጽጌን መታሰር አስመልክታ ለአሜሪካዉ ፕሬዝዳንት ባራክ አባማ ደብዳቤ ጽፋለች። ታዳጊዋ ከአባይ ሜዲያ ድረ ገጽ ዋና አዘጋጅ ጋር ባደረገችዉ ምልልስ አንዳርጋቸዉ ኢትዮጵያዊ አባት ነዉ፤ ስለ ነጻነት በታገለ እስርና እንግልት የሚገባዉ አባት አይደለም። አንዳርጋቸዉ እኔን የመሰሉ ልጆች አሉት፤ እነዚህ ልጆቹ የአባትነት ፍቅሩን ይፈልጋሉና ፕሬዚዳንት አባማ ይህንን እንዲረዱልኝና በወያኔ አገዛዝ ላይ ተጽእኖ እንዲያደርጉ ደብዳቤ እጽፌያለሁ ብላለች። ወጣት አያና መስፍን የምትባለው ታዳጊ ለአባማ በላከቸው መልእክት የግንቦት 7 ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ያስለቅቅና ኢትዮጵያን ይረዳም ብላለች።

## አንድ የአሜሪካ ሴኔተር ወያኔ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተያያዘ ዜና በጀርመን አገር የሚገኘው ለተጨቆኑ ሰዎች የመብት ተሟጋች የሆነው ድርጅት ጊዝል ሻፍት ፎር ቢድሮተ ፎልከ የአውሮፓ ህብትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ለማስፈታት ከፍተኛ ጥረት እንዲያደርጉ አሳስቧል። ለዲሞክራሲያዊቷ ኢትዮጵያ የሚታገሉት ታዋቂው የተቃዋሚዎች መሪ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ደህንነት እጅግ አሳስቦናል ሲሉ ተናግረዋል። ከአቶ አንዳርጋቸው በተጨማሪ ድርጅቱ በመግለጫ ፋሽስት ወያኔ በሃሰት ውንጀላ ለእስር የዳረጋቸው ጋዜጠኞችና የፖለቲካ እስረኞች እንዲለቀቁ ጠይቋል። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በፋሽስታዊው አገዛዝ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት ይደረጋል፤ በተለያዩ ጎሳዎች የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም በአጠቃላይ በጋዜጠኞችና በፐሬስ ነፃነት ላይ የሚደረግ ከፍተኛ ጫና አለ ስለዚህም የአውሮፓ ህብረት በኢትዮጵያ ያለው ከአንድ ቡድን የተሰባሰበ ጨቋኝ ስርአትን በመጣል ትክክለኛ ዲሞክራሲያዊ መንግስት እንዲመሰረት ጫና እንዲያደርግ እናሳስባለን በማለት የድርጅቱ የአፍሪካ ጉዳዮች ሃላፊ መናገራቸውንም ለማወቅ ተችሏል።

የተለያዩ አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና ኢትዮጵያውያን አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ የተፈጸመውን አለማቀፍ ህግን የጣሰ ድርጊት እያወገዙ እንደሚገኙ እየተከታተልን መዘገባችን ይታወሳል።

## ብአዴን ወጣቶችን "በጸረ ሰላም ሃይሎች" ላይ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ተማሪዎች ከዩኒቨርስቲ ከወጡ ድንጋይ ቀጥቃጭ ይሆናሉ፣ ድንበር ተገፋ፣ ለሱዳን መሬት ተቆርሶ ተሰጠ፣ አማራው በራሱ ብሄር ተወላጆች እተመራ አይደለም፣ የክልሉ አመራር አማራን ተሳደበ" የሚሉ ፕሮፓጋንዳዎችን በመንዛት ላይ ናቸው ሲል ሰነዱ ያትታል።ሰነዱ ወጣቶች መውሰድ ስላለባቸው እርምጃዎችም ሲዘረዝር፣ የጥፋት ሃይሎች የሚሰሩትን የጥፋት ተግባር በዝርዝር ማጥናት፣ የትግል ስልቶቻቸውን ተከታትሎ በአግባቡ መረዳት፣ይጥፋት ድርጊታቸውን ሁሉም እንዲያውቀው በርትቶ ማጋለጥ እና ሁሉም የተስተካከለ አቋም ይዞ እንዲታገላቸው መንቀሳቀስ፣ ወደ ህገወጥ ተግባር ሲሄዱም በማስረጃ አስደግፎ ለህግ እንዲቀርቡ ማድረግ" የሚሉ ነጥቦች ተቀምጠዋል። ሰነዱ በመጨረሻም "መላው የከተሞች ወጣት የጥፋት ሃይሎችን እና ጸረ-ሰላም፣ ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ልማት ተግባር ከመደበኛ ተግባራችን ጋር በማስተሳሰር በቀጣይነት መፋለም ይጠበቅብናል" ብሎአል። ብአዴን እመራዋለሁ በሚለው ክልል የህዝቡ ብሶት እየጨመረ ድርጅቱም ህዝቡን ለመምራት በማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን የብአዴን አባላት ለኢሳት ገልጸዋል።በከተሞች የሚገኙ ወጣቶችን እየሰበሰቡ " ስለ ጥፋት ሃይሎች" በየጊዜው የሚሰብኩ ቢሆንም፣ የክልሉ ወጣት ግን ብአዴንን እንደ ድርጅት እንደማይቆጥረውና አመራሩ በወጣቱ ምላሽ ተስፋ እንደቆረጡ እንዲሁም ወጣቶችን የሚያሸፍቱ ጸረ ሰላም ሃይሎችን አጋልጡ በማለት በተቃዋሚነት የሚጠረጠሩ ወጣቶችን እየሰቃዩዋቸው ይገኛሉ።

## ፋሽስት ወያኔ በአንዳርጋቸው ፅጌ ዙሪያ ያቀናበረውን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

መጀመሪያ ተያዙ በተባለበት ወቅት ተቀርፆ የተላለፈውን ምስልና ድምጽ በመጨመር የተቀናበረው ድራማ የፋሽስቱ ወያኔ ያለበትን ውጥረትና ጭንቀት የሚያጎላ እንደሆነም በስፋት የተነገረ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑ የአገዛዙን የቅጥፈት ድራማ ስህተቶችን በመንቀስ እየተሳለቁ መሆኑን ዘጋቢያችን የላከልን መረጃ ያመለክታል። በርካታ ኢትዮጵያውያን እንደገለጹት የቀረበው ድራማ የጉጅሌው ወያኔን የበለጠ የሚጋልጥ፤ ይልቁንም የስርአቱ ሹማምንት ሙያዊ ስነምግባር የሌላቸው በጣም የዘቀጡ በሰው ስቃይ የሚደሰቱ መሆናቸውን ይመሰክራል። ፋሽስቱ ወያኔ እንዳሻው በተቆጣጠረው ቴሌቪዢን ያሻውን ቢያወራ ማንም የኢትዮጵያ ህዝብ አያምነውም፤ ምንም ቢሉ ምንም ቢያደርጉ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ከቁም ነገር የሚቆጥረው አይደለም። ውሸታሞች ፤ አጭበርባሪዎች፤ ነፍሰ ገዳዮች እንደሆኑ ይታወቃል፤ ብዙ አይነት ወንጀልና ዘረፋ በአገርና በህዝብ ላይ የፈጸሙና አሁን ድረስ እየፈጸሙ እንደሚገኙ ይታወቃል፤ የፋሽስቱ ወያኔ ሹማምንቶች መሬት ነጣቂዎችና በንጹሃኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሰቆቃ በመፈጸም የሚደሰቱ፤ የዘረኝነት ሴጣን የተጠናዎታቸው ፍጥረቶች እንደሆኑም ይታወቃል፤ ባለፉት 23 የጨለማ አመታት በአገርና በህዝብ ላይ ያልፈጸሙት የወንጀል አይነት የለም። የፋሽስቱ ወያኔ ቡድን ጫካ ለነፃነት ገባን ካሉ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሚታወቀው የዘቀጠ እና ምንም አይነት ተአማኒነት የሌለው ስርአት በመሆን ነው። በጭንቀት ዛሬ ነገ ህዝብ ይነሳብኛል እያለ እየባነነ የሚኖር በክህደት ውስጥ ያለ አገዛዝ መሆኑን ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ያውቃል። አሁንም በግንቦት 7 የፍትህ፤ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ዋና ጸሃፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ ለመሰራት የሞከሩት ድራማ ይህንን አጉልቶ የሚያሳይ ነው በማለት በርካቶች ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

ፋሽስቱ ወያኔ በአቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ላይ የሰው ልጅ የማይችለውን ፍፁም አረመኔያዊ ድብደባ እያካሄደበት ነው። ይህንንም ድርጊት ቀርፆ ለህዝብ ማሳየት ጀብደኝነት አይደለም። ጋሽ አንዳርጋቸው በዚህ እድሜው ይህን አይነት ዘግናኝ ግርፋት እያስተናገደ መሆኑን ሳስበው... ልቤ ደምቶ ደምቶ ውስጤ ትልቅ የጥላቻ ኩሬ ይሰራል። ፋሽስቱ ወያኔ እየገረፈው ያለው አንድ አንዳርጋቸውን ብቻ አይደለም። በአረመኔያዊ ጅራፍ ሁሉንም ኢትዬጵያዊ እየተገረፈ እንዳለ ማሳሰብ እፈልጋለሁ። አፀፋው ምን እንደሚሆን ብታውቁ ማቅ አንጥፋችሁ በተከናነባችሁ!! የኢትዬጵያ ህዝብ " ወዬልላችሁ እናንተ የእፍኝት ልጆች! " እያለ ነው። ዛሬ ላይ የህዝብ ልጅ በሆነው በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ በግፍ የተዘረጉ ጨካኝ እጆች ነገ ላይ ሁሉም በእሳት ይማገዳሉ፤ እመኑኝ። እያደረሳችሁ ላላቹሁት ስቃይ ሁሉ ብድራቱን ትከፍላላችሁ በማለት አንድ ግለሰብ ቁጣቸውን በማህበራዊ ገፃቸው አስፍረዋል።

ሌላኛው አስተያየት ሰጭ አስተያየታቸውን ሲገልጹ ዛሬም ከኋላና ከፊት መሳሪያ ተጠምዶበት፥ የህውሃት ጅቦች ከወር በላይ ያደቀቁትን ስጋና አጥንቱን በሞገስ ተሸከሞ፤ በተደላደለ መንፈስ እንደ አንበሳ ውስጡ በኩራት ተሞልቶ፤ ማለት የፈለገውን ብቻ ተናግሮ ሲራመድ ማየት፤ የአቶ አንዳርጋቸው እናት 9 ትውለድ የሚያሰኝ ትዕይንት ነበር። አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ብዙዎች ያልደፈሩትን መንገድ በጀግንነት ተጉዞ ሚሊዮኖችን እንዳነቃነቀ፤ አሁን በጠላት እጅ ወድቆም ለሚሊዮኖች ጀግና ነው ሲሉ ለአርበኛው አንዳርጋቸው ጽጌ ያላቸውን ወደር የሌለው አክብሮት ገልጸዋል። አንዳርጋቸው ዛሬም እንወድሃለን፣ እንኮራብሃለን፥ አንተ የጀመርከውን አስፈሪ ጉዞም ለመጨረስ ቃል እንገባለን በማለት ቁጭታቸውን የገለጹም ጥቂቶች አይደሉም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዋይ ነው፤ በደንብ ይመለከታል፣ ያጤናል በመጨረሻም ፍርዱን ይሰጣል፤ በማለት በድራማው ዙሪያ ሃሳባቸውን የገለጽት ሌላኛው ግለሰብ እስካሁን የወያኔው ቴሌቪዥንና እና ጌቶቹ "አሸባሪ" ሲሉ የተሰሙት ለነፃነት መሳሪያ አንግበው በረሃ የከተቱትን ብቻ አይደለም። ጋዜጠኞችን፣ ደራስያንን፣ የሃይማኖት ሰዎችን፣ ብሎገሮችን፣ ተማሪዎችን፣ መምህራንን፣ ገበሬዎችን እና የከተማ ሰላማዊ ነዋሪዎችን ሁሉ ነው። ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz

አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ፋሽስት ወያኔ በአንዳርጋቸው ፅጌ ዙሪያ ያቀናበረውን

. . . ( ከገጽ 4 የዞረ )

የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ከእነኝህ ሁሉ ውጭ አይደለም። ይህ ማለት በፋሽስቱ ወያኔ አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ "አሸባሪ" ተብሎ ተፈርጇል ማለት ነው። ስለዚህ አቶ አንዳርጋቸው የቆሙለት ዓላማቸውን ሕዝብ የበለጠ እየወደደው፣ እያከበረው እና እየተቀላቀለው ይመጣል። በመሆኑም የድራማው ዓላማ ሙሉ በሙሉ ከሽፏል። የጉጅሌው ወያኔ "አሸባሪ" የሚለው ነፃነት ያጣውን ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ መሆኑ የታወቀ ነው። ሕዝብ በሙሉ "አሸባሪ" ሲባል ደግሞ ያለው አማራጭ አንድ ነው። ነፃነቱን ከአሸባሪ አገዛዝ መንጭቆ መውሰድ። ይህ የማይቀረው መጪው የቅርብ ቀን ክስተት ይሆናል ሲሉ በልበ ሙሉነት የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነት እያደረገ ላለው ትግል የድሉ ዋዜማ ላይ እንደምንገኝ ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜናም ፋሽስቱ ወያኔ በአገር ቤት አቶ አንዳርጋቸውን የተመለከቱ መጠይቆችን ቤት ለቤት በማዞር ህዝቡን በግዳጅ እንዲሞላ እያስገደደ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ በጠላች እጅ መውድቅ በኋላም ጭንቀት ውስጥ የወደቀው የጉጅሌው ወያኔ ጦሩን በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች እያንቀሳቀሰ እንደሚገኝና በከተማም አካባቢ በርካታ ቁጥር ያላቸው ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶችን ማስፈሩን መዘገባችን ይታወሳል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የጉጅሌው ወያኔ በጀግናው የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ በአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ላይ እየፈጸመው ያለው ግርፋትና ሰቆቃ የአላማቸው ደጋፊ በመሆን የተሰለፉ የሚሊዮኖችን ቁጣ እየጨመረና ትግሉን የበለጠ እያቀጣጠለው እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል።